# ኢሕአፓንና ሕዝቡን መደገፍ
# ወቅቱ የሚጠይቀው
# አገርን የሚያድን አሠላለፍ ነው።

*ከሐጐስ ቂናጢ*

*እግዚአብሔር አምላካችን እንዲህ ይላል።*

*"በመንገድ ላይ ቁሙ። ተመልከቱም. . . መልካሚቷ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ፤ በእርሷም ላይ ሂዱ"*

*በፖለቲካ ዓለም ብዙ ዓይነት አወደልዳዮችና ጊንጦች ስላሉ መንገድንና አሰላለፍን መለየት አገርንና ሕዝብን ያድናል። ገብረ ጉንዳን እንኳ መንገዷን ለይታ ትጓዛለች።*

*አንተ ፖለቲካን፣ ሁኔታዎችንና በይነ-ግብራዊ ስብጥርነታቸውን አልቀህ የምትረዳና ለአገርህ፣ ለህዝብህና ለኢትዮጵያዊነት ልብህንና ፖለቲካህን በቀና መንገድ የምትመራ ከሆነ እቅጩን ልንገርህ።*

*አገርህ አመፅ አርግዛ መገላገያዋ ዐናሥር ላይ ደርሳለች። ወያኔም የአመፅ ፈሳሽ አስፈርቶት ክፉኛ ታውኰ የሞት ጣር ይዞታል። ዳያስፖራ ለሕክምና በአባይ ቃሬዛ ቢመጣም ወጥመድ ደርሶበት የባሰ ቆስሎና ተቀስፎ የበለጠ እያጣጣረ ነው።*

*ሕዝብህ በባርነት ቀንበር የጠመደውን ፀረ-ኢትዮጵያ መንግሥትና ዘረኛ ሥርዓቱን ለመደምሰስ ኢሕአፓን በውስጡ አቅፎ አብሮ በሕብረት እየተዘጋጀ ነው።*

*ይህ የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ቁርጠኛ አቋምና አጣዳፊ አሰላለፍ ይጠይቃል። ስለዚህ ወገኤ ያለህ የሚያዋጣ፣ አገርን የሚያድን፣ ኢትዮጵያዊነትን የሚጠይቅ አማራጭ አንድና አንድ ብቻ ነው።*

*ይኸውም ለፀረ- ወያኔ ትግል ብቸኛና ወሳኝ ኃይላት የሆኑትን የኢትዮጵያ ሕዝብንና ኢሕአፓን መደገፍ፣ አብሮ በመሰለፍ መፋለምና ድልን አብሮ መቀዳጀት ነው።*

*ኢሕአፓ በድርጅታዊ ጥንካሬው፣ በአባላቱ ኅብረ-ብሔር ስብጥርነቱ፣ በአላማ ፅናቱ፣ በቆራጥ ትግሉ፣ በአገር ወዳድነቱና በሕዝባዊነቱ፣ በጥቁር አፍሪካ የፖለቲካ ታሪክና የአርነት ገድል ውስጥ ብቃትን ያስመዘገበና ከፍተኛ ክሬዴንሻል ያገኘ፤ ከጅምሩ ለአገርና ለሕዝብ እድገት በቅንነትና በሃቅ የተነሳ፣ መስዋዕትን በመስዋዕትነት ላይ ደርቦ ደራርቦ የከፈለ፣ ለውጭ መንግሥታት ጥቅምና ስትራተጂካዊ ትኩረት ያልተገዛ፣ በኢትዮጵያዊነቱ የታፈረና እስካሁን ድረስ ለአገርና ለሕዝብ ባልበረደ ትግል በፅኑ የቆመ፣ ገንዘብ ከማግበስበስ ፍቅር፣ ከሙስናና ከዘረፋ ቅሌት የፀዳ የሚታመን ፀረ- ወያኔ አንጋፋ*

ፓርቲ በመሆኑ፣ እንደ አይቮሪ ኮስት፣ ሊቢያ፣ የመን፣ ባህሬን፣ ሶሪያ የመሳሰሉ ፀረ-ሕዝብ ሁኔታዎች በወያኔ እንዳይከሰቱና ጥፋቶች እንዳይከተሉ ብቃት ያለው አመራር መስጠት፣ ድልን ማቀዳጀትና አገርን ማዳን ይችላል።

ይህን የሚታመን፣ የሚያዋጣ፣ አንጋፋና መሪ ኃይል ከመደገፍ መቆጠብ ከንቱ ! ከንቱ ! ከንቱ ! የሆነ የፖለቲካ ግብዝነት ነው። በጆን ማኬን አባባል የፖለቲካ ናይቪቴ ማለት ነው።

ስለዚህ ለአገርህ፣ ለሕዝብና ለኢትዮጵያዊነት በፀረ- ወያኔ እረድፍ በሃቅ የቆምህ ሁሉ ከደካማ አመላካከት፣ ከገልቱ ስሜት፣ ከከረረ ጥላቻ፣ ራስን ከመውደድ፣ ከፍራቻ፣ ከሌሎችም ጐታችና ሐኬተኛ ስበቶች ራስህን በማላቀቅ ለወሳኙ ድል በአጣዳፊ በኢሕአፓና በኢትዮጵያ ሕዝብ ዙሪያ ደግፊህ በመሰበሰብ መደራጀትና መታገል ያዋጣሃል።

"ልባም ሴት ለቤቷ ክንዱን ታበረታለች"

አንተም የምትወዳት አገርህ የባሰ ጭንቅ ላይ እንዳትወድቅ፣ ልጆችህም ግፍና ባርነት ወርሰው እንዳይወለዱ፣ ለሕዝብህ፣ ለሰንደቅ ዓላማህ፣ ለኢትዮጵያዊነትህ፣ ለክብርህ ለብሔራዊ ኩራትህ፣ ለደህንነትህ፣ ለዕድገትህ፣ ለደስታህ፣ ለቤተሰብህ፣ ለሚስትህ፣ ለመብትህ፣ ለነፃነትህ፣ ለሰላምህ፣ ለሕልውናህ ስትል አሰላለፍህን አስተካክል።

ሰልፍ ብቻ አይበቃም። ያለ - የሌለ ጊዜህን፣ ጉልበትህን፣ እውቀትህን፣ ሃብትህን፣ ወዘተ. . . ሁሉ ማፍሰስና መረባረብ አለብህ። ወቅቱ ለሚጠይቀው ትግልና በተቃዋሚ ስም በስውር ለሚሸረበው ሴራና እንቅስቃሴ ክሽፈት መፍትሄውና መንገዱ ይኸው ነው።

*ኢትዮጵያዊነት ያሸንፋል !*

*የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።*